


የመጽሐፉ ርዕስ ፡ “***ፍጹም ነው እምነቴ***”

ደራሲ ፡ አቶ ነሲቡ ስብሐት

ገጽ ብዛት ፡ 400 ከመጽሐፉ ድምጽ ትረካ ሲዲ ጋር

አስተያየት ፡ ትዕግስት ዓለሙ

<u>“***ፍጹም ነው እምነቴ***” ከትውልድ ለትውልድ የተላለፈ</u>

በቅድሚያ የመጽሐፉን ደራሲ አቶ ነሲቡ ስብሐት ለዚህ ታሪካዊ መጽሐፋቸው ምስጋናዬንና አድናቆቴን በመቻር ይህን መጽሐፍ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ያነበው ዘንድ ስለመጽሐፉ ያለኝን አስተያየት በአጭሩ አቀርባለሁኝ።

“***ፍጹም ነው እምነቴ***” መጽሐፍ ሁሉንም የስሜት እዋሳት እያንቀሳቀሰ ቁምነገሮችንና መልዕክቶችን አጠገቦ እንደተካሄደ ያህል ቁልጭ አድርጐ ያቀርባል። መጽሐፉ በቁምነገር ውስጥ ቀልድን፣ በቀልድ ውስጥ ቁምነገርን ይዞ መጀመሮን ሳያውቁ አንብበው ይጨርሱታል። የመጽሐፉ ለቅሶ ሳያስቡት እንባ በጉንጭ ያፈሳል፣ ንዝረቱ እንደ ኤሌትሪክ ነው፣ ግርፊያው ያማል፣ ግድያው አፍ በደም ይሞላል፣ ስቃዩ እንቅልፍ ያሳጣል። እውን ደርግ ፋሺስት ነው አይደለም? ለሚለው መልስ “***ፍጹም ነው እምነቴ***”ን መጽሐፍ ላነበበ ከበቂ በላይ ምላሽ ይገኝበታል።

አቶ ነሲቡ ስብሐት ሁላችንም የምንጋራውን ልጅነትን በውብ የስነጽሁፍ አገላለጽ መስጠውን ኢሕአፓ ማነው? አሠራሩ፣ አደረጃጀቱ፣ ትግሉ እንዴት ነበር? ምን ይመስል ነበር? የሚለውን ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ አይደለም በድርጅቱ ውስጥ ነበርን የያ ትውልድ ታሪክ ተጋሪዎች ነን ለምንለው እንኳ ብዙ የማናውቀውንና የዘነጋነውን የዛሬ 40 ቀን የሆነ ያህል አስቀምጠውልናል። በያንዳንዷ ትረካቸውና አገላለጻቸው የጸሐፊው የማስታወስ ችሎታ ሊደነቅ ይገባዋል።

አቶ ነሲቡ ስብሐት በመጽሐፋቸው ያስቀመጡት የኢሕአፓ አወቃቀርና የመዋቅሩ ገለፃ ለመጀመሪያ ጊዜ በግልጽና በሚገባ አገላለጽ አስቀምጠውታል። ወደፊት ይህ አወቃቀር ለሀገራችን አይደለም በዓለም ደረጃ ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች በዋቢነት እንደሚጠቀስ አድርገው ዘላለማዊ ጽሁፍ አቅርበዋል። አደፍርስ ምንድነው? የኢሕአፓ ልሳንስ ዴሞክራሲያ? ጎህ መጽሔት፣ ኮድ፣ ኡ ኡ ታ ኮሚቴ፣ ሞባይል ቲም፣ አንጃ ወዘተ እንዴት አድርገው እንደገለጿቸው ለማወቅ “***ፍጹም ነው እምነቴ***”ን ያንቡ።

በዚያ ጊዜ የእሳቸው ዕድሜ እኩያዎች በየቀበሌው፣ በየወጣት ማህበሩ፣ በመሠረተ ትምህርቱ ከሚወዱትና ከሚያፈቅሩት ነዋሪዎቻቸው ጋር ኢሕአፓን ለማስተዋወቅ ትግሉን በድል ለማጀብ ያደረጉትን ተጋድሎና የከፈሉትን መስዋዕትነት ፍጹም የሕዝብ፣ ፍጹም የሀገር፣ ፍጹም የድርጅት፣ እምነት በትክክለኛና በሚገባው ርዕስ “***ፍጹም ነው እምነቴ***” ብለው ገልጸውታል።

በየቀበሌው የነበረውንና እናቶች በትግሉ ያደረጉትን አስተዋጽዎና ተጋድሎ ለአርኣያነት እማማን እስከፎቷቸው በማስቀመጥ የቀረበው ትረካ ዓይኔ እምባ እየረጨ እንዳነበው ተገድጃለሁ። ከመጽሐፉ የወሰድኩትን የእማማን ንግግር ከመጽሐፉ ገጽ፡158 ልጥቀስ

*“ወገኖቼ” አሉ ለስለስ ባለ ድምፃቸው “ወገኖቼ ልጆቻችንን ሰጠን የቀሩትንም መግቢያ መውጫ አሳጧቸው፣ የት እንድረስ፣ ሰው በሀገሩ፣ ሰው በሰፈሩ፣ እውን እነኚህ አብረውን ኖረዋል? አብረውን በልተዋል? አብረውን ጠጥተዋል? ምነዋ ልጅ ማየት አስጠላቸው? ምነዋ ልጅ ሲያዩ ይጐመዠሉ? እኛው መርጠናቸው እኛኑ ያሳድዳሉ። ልጆቻችንን ከእቅፋችን እየገደሉ የተረፉትንም እያሳደዱ ብቸኛ አድርገውናል። ስንበላ ስንጠጣ ትካዜ ነው፣ ለሊት የነሱን ኮቴና ኮሽታ ስናዳምጥ እንቅልፍ የለም፣ ወጣት ፍለጋ ቤታችንን ይዞሩታል፣ የት እንድረስ የት ይሂዱ? ወገን ኧረ በቃን! ተነሱ! ከዚህ በላይ ምን ልንሆን ነው? በሀገራችን በቀያችን፣ በመንደራችን መኖር ከነሱን የሚፈለገው ሁልሽም ማማሰያሽን ይዘሽ ውጭ፣ ሀገራችን ለልጆቻችን ካልሆነች ምን ሕይወት ይኖረናል ጎበዝ ተነሱ! እንነሳ!...”*

ይህንን ያነበበ “***ፍጹም ነው እምነቴ***” መልዕክቷ የትናንቱን ብቻ ሳይሆን ዛሬስ? ብለን እንድንጠይቅ የያ ትውልድን ታሪክ ለዛሬ ትውልድ አቅርባለች።

አቶ ነሲቡ ወጣቶችን ዋልታ አድርጎ ከታዳጊ ሕፃናት እስከ አዛውንት ያካተተውን የአንድ አካባቢን ኢሕአፓ የትግል ታሪክ እንደ አብነት ***በ"ፍጹም ነው እምነቴ***" መጽሐፋቸው ሲያስነብቡን በታዳጊ ሕፃናት ሆያ! ሆዬ! ዝማሬ አጅበውታል።

የየኔታን ሀ…ሁ… ቆጥረው ያደጉት አቶ ነሲቡ ስብሐት በእሳቸው አባባል "የእናታቸውን እቅፍ ያልጠገቡ ታዳጊዎች" ለሀገርና ሕዝባቸው ነፃነት ፋና ወጊ በመሆን "ትምህርት ከድል በኋላ" ብለው ከስምንተኛና ዘጠነኛ ክፍል ሙሉ በሙሉ ወደ ትግሉ የተቀላቀሉት ታዳጊዎች የሕዝብ ድል በደምና በሬሳ ታጅቦ ተስፋቸውን ደርግና ካድሬዎቹ በልተውት የቁጭትና የምሬት አባባላቸው

"ከድል በኋላ ያሰብነውን ትምህርት "ከሞት" በኋላ ለመቀጠል የተገደድን የኢሕአፓ ልጆች ከባድ ፈተና ውስጥ ወደቅን።" (ገጽ 336) በሚል ሲገልጡት ስሜትን ያናውጣሉ፣ መንፈስን ይረብሻሉ።

"***ፍጹም ነው እምነቴ***" መጽሐፍ እያንዳንዷ ገጽ ላይ የተቀመጠው አባባል ስሜትን ይነካል፣ ደጋግማችሁ አንብቡኝ ያሰኛል። የመጽሐፉ የእያንዳንዱ ርዕስ መልዕክት ትምህርት የሚቀሰምበት ነው። ይህ መጽሐፍ በደርግና መኢሶን ተሰልፈው የነበሩ ኃይሎች በሚገባ ሊያነቡት ይገባል። የታሪኩ ባለቤት በኢሕአፓ ውስጥ ያለፉና ያሉ ሊማሩበት ይገባል። መጽሐፉ ለትውልድ የሚተላለፍ የታሪክ መረጃ እንደመሆኑ ቤት ለቤት አሰሳ፣ ነፃ እርምጃ፣ ቀይ ሽብር፣ ቀበሌ፣ ገበሬ ማህበራት፣ ደርግና መኢሶን ማንና ምን እንደነበሩ የአሁኑ ትውልድ ግንዛቤ ይጨብጥ ዘንድ ቀለል ባለ ቋንቋ በመቅረቡ መጽሐፉን በማንበብ እውን ኢሕአፓ ማነው? ለሚለው የተሰጠውን ምላሽ እንድንነጋገርበት፣ እንድንወያይበት ይጋብዙንናል።

"***ፍጹም ነው እምነቴ***" እስከዛሬ ስለ ኢሕአፓ ከተፃፉ መጽሐፍት በሙሉ ከድርጅቱ አሠራራ ከትግሉ አካሄድ ጀምሮ የማናውቃቸውን በርካታ ቁም ነገሮች የያዘ መጽሐፍ በመሆኑ ሊነበብ ይገባዋል።

ከልጅነት ጀምሮ እስከ ደርግ ቀይ ሽብር ግድያ ያለውን ታሪክ መልዕክት ባላቸው ሥዕሎች መታጀባቸው መጽሐፉን ከተራራው ጫፍ ያስቀምጠዋል። በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሥዕሎች እራሳቸው ከጽሁፉ ያልተናነሰ መልዕክት አላቸው። እንደምሳሌ በገጽ 210 የተቀመጠው "ሥዕል 10. ቤተሰብ እስረኞችን ሲጠይቁ" የሚለው አተኩሮ ላየው እራሱን የቻለ ምንባብ ነው። ከጽሁፉ እንደተረዳሁት በግድያ ማግስት ቤተሰብ ስንቅ ይዘው መጥተው የልጆቻቸውን የግድያ መርዶ ሲሰሙ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ይመስላል። በጊዜው የነበረውን ሰቆቃ፣ ለቅሶና ዋይታ ቀርጾ ያስቀረ ሥዕል። የግድያ ማግስት በመሆኑ አሞሮች ሬሳና ደም አይተው "የወጣቶች እናት ታጠቂ በገመድ፡ ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ" እንደተባለው ወጣቶችን ሊቀብሩ ሲያንዥብቡ በሥዕሉ ተካቷል። ሊታዩ የሚገባቸው አመርቂ ሥዕሎች "***ፍጹም ነው እምነቴ***" አካቷል።

ሌላው "***ፍጹም ነው እምነቴ***" መጽሐፍ ልዩ የሚያደርገው በኢትዮጵያ ደራሲያን ከወጡ መጽሐፍት ባልሳሳት የመጀመሪያው ከነ ሙሉ የመጽሐፉ ትረካ ጋር የተካተተ ሲዲ አብሮ መኖሩ አንዱ የመጽሐፉ ውበት ነው። አቶ ነሲቡ የራሳቸውን መጽሐፍ አንዳንድ ቦታ እገዛ ካደረጉላቸው ቤተሰብ አባላት በላቀ መልኩ በራሳቸው ድምጽ ይህን ወደ 12 ሰዓት የሚፈጅ ትረካ ለትውልድ ያበረከቱ የመጀመሪያ አኩሪ ዜጋ ናቸው።

አቶ ነሲቡ በዚህ ታሪካዊ መጽሐፋቸው የመጽሐፋቸው ዋና አንኳር ስለሆነው "ቀይ ሽብርና ከፍተኛ 15 እስር ቤት ታሪክ" በክፍል ሁለት እጅግ ሥዕላዊ በሆነና ሰውነትን በሚነዝር መልኩ የሰውን ልጅ መከራ ቻይነት በአንድ በኩል ሲገልጹ የሰውን ልጅ አውሬአዊ ባህሪ ደግሞ በሌላ መልኩ ሲተርኩ በመጽሐፋቸው ገጽ 250 እንዲህ ይሉታል

"የከፍተኛ 15 እሥር ቤት ታሪክ በእያንዳንዱ ላይ የደረሰው መከራና ግፍ ቀላል አልነበረም። በከፍተኛ 15 የሰው ልጅ ምን ያህል መከራ ቻይ መሆኑ ታይቶበታል። የከፍተኛ 15 ስቃይ በሆሊውድ ፊልሞች ላይ በልብ ወለድነት በተሠሩ ፊልሞች ላይ የታዩት በተግባር ታይተዋል። ከፍተኛ 15 ሊታመን የማይችል መንፈሳዊ/ስፐሪቱአል ክስተት በዮናታን ታይቷል። የከፍተኛ 15 ስቃይ ከእስር ቤት ከተወጣም በኋላ በርካታዎችን አካል ጉዳተኛ፣ የአዕምሮ በሽተኛ፣ መካን፣ የስነ ልቦና ሰለባ ጥቃተኞች አድርጓል። በተቃራኒው ደግሞ የሰው ልጅን ጭካኔና ድብቅ አውሬያዊ ባህሪ እንዳለን በገዳዮቻችንና በገራፊዎቻችን አይተናል። ከእኛው ጋር ኢሕአፓ የነበሩ ሊታመን በማይችል መልኩ አረመኔ ገራፊዎችና ገዳዮች ሆነውብናል። እነ ከፈለኝንና በላይን ያየ በአጭሩ የሰው አውሬነታቸውን ይመሰክራል። አረመኔዋን መስታወት የሚያውቅ፡ ሴት ልጅ እውን እንዲህ ዓይነት ጭካኔ ይኖራት ዘንድ እግዜር ሳይሆን እራሱ ሰው እንደፈጠራት፣ እንደሠራት ሊከራከር ይችላል።"

"***ፍጹም ነው እምነቴ***" የደርግን ቀይ ሽብር ዘመቻ በዚህ መልክ ያስቀምጠዋል

ገጽ 211

*"ቀይ ሽብር እውን የሰው ልጅ እንዲህ ዓይነት ድብቅ ባህሪ አለውን አሰኝቷል? እውን ሰው በሰው ላይ አውሬ ይሆናልን? ሰው ሰውን ለማሰቃየት ያለው አቅምና ጉልበት ከምንም በላይ እንደሆነ ደርግና ካድሬዎቹ አሳይተውናል። ልጅን ገድሎ እናትና አባቱ በራፍ አስከሬን መጣል፣ አይተውም እልል ይሉ ዘንድ ማስገደድ ተደርጓል። የገደሉትን አስከሬን ሌሎች አብሯቸው እንዲያድር አድርገዋል። የአንድ ቤተሰብ ወንድማማቾችን፣ እህትማቾችን፣ ወንድምና እህትን ገድለዋል። የሕፃናትን አባትና እናት ገለው አውላላ ሜዳ ላይ ጥለዋል። ይህ ሁላ ግፍ ታዲያ የተካሄደው ይበልጥኑ ሁሉንም አስረው በቁጥጥር ሥር ካዋሉ በኋላ ነበር። የእስረኛውን ምግብ እየበሉ፣ ልብሱን እየተላበሱ ሲገሉ ሊኖሩ መፈክራቸው "ቀይ ሽብር ለዘላለም ይኑር" ነበር። በየሳምንቱ መግደል መደበኛ ሥራቸው ይሆን ዘንድ ጥረዋል። ከፖለቲካው ባሻገር በቂም በቀል፣ በመንፈስ ቅናት፣ የተመኟትን ለማግኘት የስንቱን ቤት ዘግተዋል።"*

አቶ ነሲቡ ስብሐት በልጅነታቸው አብረው ያደጉት የካዛንችስ እኩያ ጓደኞቻቸው በተፈጠረው የዓላማ ልዩነት እንዴት እንደተለያዩና ሁኔታውም በፈጠረው ክስተት ፀፀታቸውን በማሰማት ዳግም እንዴት እንደተገናኙ ማሳየት ብቻ አይደለም አብሮ አደግ የመኢሶን ጓደኛቸውን በምስክርነት በመጽሐፋቸው አካተዋል።

የአቶ ነሲቡ መጽሐፍ አንባቢ እንዳይሰለቸው ልብ እያንጠለጠለ የተረኩት የልጅነት የፍቅር ሕይወታቸው ትረካ ከትግሉ አኳያ እያዛመዱ ያቀረቡት በፍቅር ውስጥ እምነትን ሲገልጹ ትግሉን፣ ኢሕአፓን እንዴት አድርገው እንዳስቀመጡት ለመረዳት መጽሐፉን ካልቃኙት ማስረዳት ይከብዳል።

ስለ "***ፍጹም ነው እምነቴ***" በዚች አጭር ጽሁፍ ሊገመገምም ሆነ ሊፃፍ ቦታ አይበቃውም። በእርግጠኝነት ልናገር የምችለው ግን ይህ መጽሐፍ በዓፄ ኃ/ሥላሴ ዘመን የነበረውን ሥርዓት ገጽታ በታሪካዊ ልብ ወለድነት ደራሲ አዲስ ዓለማየሁ "***ፍቅር እስከ መቃብር***" በሚለው መጽሐፋቸው እንዳስነበቡን ሁሉ አቶ ነሲቡ ስብሐት የታሪኩ ተዋንያንን ስም ለመጥቀስ ከአደረጉት "ድፍረት" ጋር በከፍተኛ 15 ቀይ ሽብር እውነተኛ ታሪክ መጽሐፋቸው የደርግን አገዛዝ ማንነት ያስቀመጡበት ታሪካዊ መጽሐፍ መሆኑን ልመሰክር እችላለሁ። ለዚህም አቶ ነሲቡ ስብሐት ታሪካዊ ግዴታዎን ተወጥተዋል። ዛሬ በእርሶ መጽሐፍ ሰማዕታት ወገኖቻችን አሸንፈዋልና ደስ ይበልዎት። "***ፍጹም ነው እምነቴ***" መጽሐፍ ገና በርካታ ውይይቶችን በመቀስቀስ መጽሐፉ ለወደፊት ታሪክ አጥኚዎችና ተመራማሪዎች የቀረበ፣ ከትውልድ ለትውልድ የተላለፈ የሀገር ገጸ በረከት በመሆኑ እንኳን ደስ ያሎት እላለሁ።

የጽሁፌ መቋጫ የማደርገው ደራሲው በራሳቸው ላይ ስለደረሰው ግርፊያ፣ ግፍና መከራ በገጽ 186

*"ለቆሙለት ዓላማ መፈተኛው ሰዓት ደረሰ። "ፍጹም ነው እምነቴ ለትግሉ ነው ሕይወቴ" ዝማሬ በተግባር ለጥያቄ ቀረበ።" "በትግል መሞት ሕይወት" ከፊቴ ቆመ። ዱላው ጀመረ።"*

በሚል ካስነበቡን በኋላ የነበራቸውን ጥንካሬና ጽናት በገለጹት በገጽ 190 በአስቀመጡት አባባላቸው ይሆናል፡

"የድርጅቴን ሚስጥር ጠብቄ፣ ውድ የትግል ወንድሞቼንና እህቶቼን ሳልጠቁም እራሴን ለመስዋዕትነት ማቅረብ የመሰለ ታላቅ ስም የለምና በውስጤ ሞቴ የሚቀርብበትን ሰዓት መማጸን ያዝኩኝ። ትግሉ እንዲቀጥል፣ የድሉ ቀን እንዲቀርብ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልተሸራረፈ መብቱን እንዲጎናጸፍ፣ የላባደሩ ፓርቲ ኢሕአፓ ለድል በቅቶ ሕፃናት በቀያቸው ቦርቀው እንዲያድጉ፣ ወጣቶች የጮኹለት ላብ አደርና አርሶ አደር በሀገሩ እኩል መብት ኖሮት ደስ ብሏቸው ሀገራቸውን እንዲያይዋት፣ እናት አባት አዛውንቶች ልጄ የት ደረሰ፣ በደህና ይመጣ/ትመጣ ይሆን ከሚል የሰቀቀንና የስጋት ኑሮ ተላቀው፣ በሀገራችን የፆታና የሃይማኖት እንዲሁም የብሔር/ብሔረሰቦች እኩልነትና መብት ተከብሮ፣ ምሁራን ለሀገራችን በልማትና ዕድገት ጎዳና መዝለቅ በሙያቸው ምርምራቸውን ቀጥለው አቅጣጫ ያሲዙ ዘንድ፣ ሀገራችን የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገር ሆና ግፍና፣ መከራ፣ ድንቁርና፣ ድህነት፣ በሽታ በነበር የሚወሱበት ጊዜ ይመጣ ዘንድ ለተጀመረው ትግል ደማችን ውኃ፣ አጥንታችን ዋልታ ይሆነው ዘንድ ቃል ኪዳን አለብንና ነው "የታጋይ እረፍቱ ሞቱ" ያልነው።"

"***ፍጹም ነው እምነቴ***" ማንም ኢትዮጵያዊ ሊያነበው የሚገባ መጽሐፍ

ትዕግስት ዓለሙ tegistalem@yahoo.com

ታህሳስ 2007 ዓ.ም.